የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 24
ADDIS ABABA 13th February 2009

ማውጫ

ደንብ ፻፷፪/፪ሺ፩

የመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..............................ገፅ ፬ሺ፭፻፲፰

CONTENTS

Regulation No. 162/2009

Irrigation Development Investment Incentives Council of Ministers Regulation.................................... Page 4518

## ደንብ ቁጥር ፻፷፪/፪ሺ፩

## ስለመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርእስ

ይህ ደንብ "የመስኖ ልማት ኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፷፪/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተደነገጉት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፫/ "የመስኖ ልማት" ማለት ከ፶ ሄክታር በላይ የሆነ የመስኖ ልማት፤

፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## *Regulation No. 162/2009*

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR IRRIGATION DEVELOPMENT INVESTMENT INCENTIVES*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 9 of the Investment Proclamation No. 280/2002.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Irrigation Development Investment Incentives Council of Ministers Regulation No. 162/2009".

2. *Definitions*

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Investment Proclamation No. 280/2002;

2/ The definitions provided under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

3/ "Irrigation development" means irrigation development covering more than 50 hectares of land;

4/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፰. <u>ጥናትና ዲዛይን የተጠናቀቀላቸውን ፕሮጀክቶች ዝግጁ ስለማድረግ</u>

በመስኖ ልማት ዘርፍ የሚሠማራ ባለሀብት በመንግሥት ወጪ ጥናትና ዲዛይን የተጠናቀቀላቸውን ፕሮጀክቶች በነፃ ወስዶ መጠቀም ይችላል፡፡

፱. <u>የመስኖ ልማት ዋና ስትራክቸሮችን ዝግጁ ስለማድረግ</u>

መንግሥት በመደበኛ የልማት ፕሮግራሙ ባለማቸው የግድብ፣ የዋና ዋና ቦይና የመጋቢ መንገድ ግንባታዎችን የመሳሰሉ የመስኖ ልማት የሚገባ ባለሀብት በመንግሥት ሲተጠቀሱት ስትራክቸሮች ግንባታ የወጣውን ወጪን መተካት አይጠበቅበትም፡፡

፲. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

፲፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

8. *Availing Projects with Completed Feasibility Study and Design*

An investor who wants to invest in irrigation development sector may, free of charge, take and use government financed feasibility studies and designs of irrigation development projects.

9. *Availing Major Irrigation Structures*

An investor who wants to invest in irrigation development using major irrigation structures such as dams, main canals and access roads developed under the regular development program of the Government may not be required to pay back the investment cost covered by the Government.

10. *Power to Issue Directives*

The Ministry of Water Resources may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

11. *Effective Date*

This Regulation shall come into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 13th day of February, 2009.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA